# ከዋናው መስሪያ ቤት የመጡት እንግዳ

ከበልጅግ አሊ

በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ተከታታይ ልብ ወለድ ታሪክ

ዘመኑ ካለ እሳቸው አመራር ምንም ነገር አይሳካም የተባለበት፣ እሳቸውም ደግሞ በየመንግስት እርሻው እየሄዱ የሚሳደቡበት፣ በየእርሻው ላይ የሚሰራው ሰራተኛ እርሻው ተዘግቶ ከስራ ተፈናቅሎ ቤተሰቤ ይበተናል ብሎ ጭንቀት ውስጥ የገባበት፣ እሳቸው በማያውቁት እየገቡ የሚወስኑበት ፣ እኛ እሳቸውን ለማስደሰት ምንም የማናደርገው ነገር የሌለበት፣ እሳቸው በእኛ እንደዛ መሆን የሚደሰቱበትና የሚሳለቁበት፣ ቆራጡ ቆራጥነታቸውን እኛ እኛነታችን የታወቀበት ዘመን ነው።

ቦታው ሰማዩ ያረጀበትና ወሃ አለማቋረጥ ይለቅ የነበረበት፣ ደን ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍለ ሃገር በዛ ብሎ የሚገኝበት፣ የኢሊባቡር ክፍለ ሃገር ነው። ከጎሬ ከተማ ወደ ጋንቤላ መንገድ ትንሽ አለፍ ብሎ የሚገኝ ሲሆን ጉመሮ ተብሎ የሚታወቀው የሻይ ተክል ያለበት ነው። ያ ያረጀው ሰማይ እንኳን ሳይቀር ደክሞት በእሳቸው ዘመን ስራውን ስላቋረጠና ውሃ መልቀቁን ስላቆመ በተፈጠረው ድርቅ ምክንያት በዛ ዘመን የተተከለው ሻይ ሰለደረቀ እሳቸው ከመጡ ቆራጥ አመራር ይሰጡበታል ተብሎ ሁሉም ሰራተኛ እንቅልፍ ያጣበት ወቅት ነው።

ከጉመሮ አጠገብ በሳምንት አንድ ቀን ገበያ የሚቆምባት እሮብ ገበያ የምትባል ትንሽ ደረቅ ከተማ አለች።ጠጅ ቤት፣ ካቲካላ መሸጫ፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ሱቆች እከተማው ውስጥ ይገኛሉ። የብዙዎቹ የጉመሮ ሰራተኛ ልጆች አንደኛ ደረጃን ትምህርታቸውን እዛ ተምረው ሁለተኛ ደረጃን ጎሬ ሄደው ይማራሉ።የጎሬ ከተማ የተመሰረተው ተራራ ላይ በመሆኑ ወደ ጎሬ ለመሄድ ዳገትነት ሰላለው አድካሚ ነው።ከጉሬ ወደ ጉመሮ ሲጓዙ ጉመሮ ከመደረሱ በፊት አንድ ትንሽ ወንዝ ማቋረጥ ያስፈልጋል የወንዙ ስምም ጉመሮ ነው።

ዕሮብ ገበያ ቀን ቀን ባዶ ሆና ብትውልም ማታ ማታ ግን በሰራተኛው ትሞላለች። ጠጅ የሚፈልገው ፣ ጠላም ያማረው ፣ ጨዋታም ይሁን ወሬ መለቃቀም የፈለገ ወደ እሮብ ገበያ ያቀናል። አንዳንድ ግዜ ጨዋታው ይደራል፣ አዝማሪው ይጫወታል፣ ክርክርም ይነሳል፣ ድብድብም ፣ አምባጓሮም ፣ የተለመደ ክስተት ነው።

በጉመሮ ሻይ ልማት ውስጥ ቋሚና ግዜያዊ የሆኑ ሰራተኞች ይገኙበት ነበር። የሰራተኛው ቁጥር እንደ ዝናቡ መጠን ይቀያየራል። ዝናቡ በበዛ ወቅት የሻይ ተክሉ ቶሎ ለመለቀም ስለሚደርስ የሰራተኛው ቁጥር ይጨምራል። ሰራተኞቹ መስሪያ ቤቱ በሰራላቸው ቤት ውስጥ ይኖራሉ። ቋሚ ሰራተኞች የተሻለ እንክብካቤ ሲኖራቸው ጊዜያዊዎቹ በቀን አንድ ብር ከዘጠና ሁለት ሳንቲም እያገኙ ይኖራሉ ። ለሰራተኞቹ ምግብ የሚሆን በቆሎ ድርጅቱ እያመጣ በአነስተኛ ዋጋ ያከፋፍላል።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ ካሉት መምህራን መካከል አንድ ተስፋዬ የሚሉት የቀይ ዳማ የሆነና ፊቱ ጢም የተሞላ አስተማሪ በከተማዋ ውስጥ በጣም ተዋቂ ነው። ተስፋዬ እከተማ በሚገኘው ጠጅ ቤት ውስጥ አይጠፋም ። ጠጅ ቤት የገባ የወጣው በሙሉ ሰላም መምህር ይሉታል።ተስፋዬን የከተማው ሰው በሙሉ ሊቁ ብለው ይጠሩታል። ሊቁ የተባለበት ምክንያት አንድ በጨርቅ የተሸፈነች ራዲዮ አብራው አትለይም ነበር።ታዲያ ሙሉ ሰአት እየጠበቀ በእንግሊዘኛ የቢቢሲን ዜና ያዳምጣል። ቢቢሲ የሚሰማውን የእንግሊዘኛ ዜና ለጠጅ ቤቱ ደንበኞች ስለሚያስረዳቸውና ሁሉም ሰለሚደነቁ ሊቁ ብለውታል።ሊቁ ታዲያ ሲሰክር ማልቀስና መጮህ ጠባዩ ነው። ሊቁን በጣም የሚያውቁት ሰዎች ጠዋት ጠዋት መካሪ ፣ ከሰአት በኃላ አጫዋች ፣ ማታ ማታ ጨኺና ሰው የማይነካ ሰላማዊ ነው ይሉታል። ሊቁ ምንም እራሱን መደበቅ ቢፈልግም የአካባቢው ሰው እንደሰካራም ሳይሆን እንደ አዋቂ ይቆጥሩታል። አንድ በጣም የሚያስጨንቀው ጉዳይ አለ ብለው ስለሚያምኑ ሁል ግዜ እሱን ይንከባከቡታል። በትምህር ቤቱ ውስጥ ግን በጣም የተከበረና ስነ ስርአት ያለው ሰው እንደሆነ የታወቀ ነው።

ሊቁ ለምን ከአዲስ አበባ እንደወጣ እራሱም ባይናገርም አንዳንዴ ሲሰክር የቴዲ አደባባይ ልጅ ነኝ። እዚህ እንዲህ ሰካራም መሆኔን አትመልከቱ። ስንቱን እማንቀጠቅጥ ነበርኩ ማለትን ይወዳል።በዛ ዘመን ከቀይ ሽብር ያመለጡ ወጣቶች አስተማሪ እየተቀጠሩ በየገጠሩ የሚገኙ ስለነበር  እሱ በዛ ይጠረጠር እንጂ ማንም ስለሱ ማንነት በግልፅ የሚውቅም የሚከታተለውም ደግሞ አልነበረም።

ሊቁ ራዲዮዎኑን ይዞ መጠጥ ቤት በገባበት ግዜ በየሙሉው ሰዓት ጸጥታ እየተጠየቀ ሊቁ ዜና እንዲሰማ ይደረጋል እንጂ ሊቁ ከተቀመጠበት ቦታ አይነሳም። ሊቁ ዜናውን ከሰማ በኃላ ለሌሎቹ ያስረዳቸዋል ። ስለ ቀዝቃዛው ጦርነት ፣ ሰለ ኮሚኒስቶች ፣ ስለ አሜሪካ  ብዙውን ግዜ የሚያስረዳውና የሚወደው አርዕስት ነው። አንዳንዴ የአማርኛ ፕሮግራም ሲኖር ሊቁ ራዲዮኑን ጮክ አድርጎ ይከፍተዋል። ታዲያ ራዲዮኑ እንደምን አመሻችሁ ስትል በጠጅ ቤቱ የሚጠጡት ሁሉ እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ። ሊቁ ራዲዮኑን ጮክ አድርጎ መክፈት አይወድም። ራዲዮ ጮክ አድርጎ መክፍት ድንጋይ ይጨርሳል ብሎ ስለሚያምን ዝቅ አድርጎ ነው የሚከፍተው። አንዳንዴ ድምፁ ያልተሰማቸው  ድምጹ ድንጋይ አይበላም ካሉት  ለመሆኑ የኒወተንን ቴርሞ ዲናሚክ ስለ ሃይል የፃፈውን አንደኛ ህግ ታውቃለህ  ብሎ ይጠይቃል። ስውየው ኒውቶን ማን እንደሆነ አላውቅም ካለው ታዲያ ጠይቅ እንጂ አትቃወም ብሎ ዝም ያሰኘዋል ።ሌሎቹ ደግሞ እስቲ እንሰማበት በኃላ ያስረዳሃል ብለው ተናጋሪውን ዝም ያሰኙታል።

ከየት እንደመጣው ወይም እንደነበበው አይታወቅ እንጂ ተስፋዬ የሚልም ግጥም አለው።

እናትና አባቴ እጅግ ቢራቀቁ  
አንድ ስም ሰጥተውኝ ተናግረው አበቁ  
ልጅ ተስፋ ነውና ተስፋዬ ብለውኝ  
ቆሜ እንድጠራቸው በግልጽ አደራ አሉኝ፡፤  
አባቴም ለራሱ እያለኝ ተስፋዬ  
እናቴም ለእራሷ ስትልኝ ተስፋዬ  
ተስፋቸውን ጣሉ በነገው ተስፋዬ።

ሁል ግዜ ምሽቱ እየመሸ ሲሄድ ሊቁ መጠጡ በዝቶበት እንደተለመደው እየጮኸ „ እኔ ያራዳው ልጅ እዚህ ልቅር። ስላላወቃችሁኝ ነው እንጂ የሊግ አባል ነበርኩ“ እያለ ወደ ቤቱ ሲሄድ የሰሙ ሁሉ ሊቁ የሊቆች አባል ነበር እያሉ ያወሩለት ነበር። አካባቢው በጣም እሩቅ ሰለነበር ሊቁ የሚለው ሊግ ምን እንደሆነም አያውቁምትም እንጂ ሊቁ በጣም የሚወደውና የሚያፈቅረው ጉዳይ እንደነበር ሁሉም ይገምታሉ። አንዳንዴ ሲከፋው አከተማው መውጫ ላይ ያለው ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ጮክ ብሎ አዲስ አበባ ቤቴ ብሎ ይዘፍናል።

ሊቁ መጀመሪያ ወደዚህ አገር ሲመጣ አፍሮና የከተማ ልጅ ፣መጠጥ ባፉ የማይቀምስ ሲሆን በጣም ብዙዉን ጊዜውን የሚያሳልፈው መፃህፍት በማንበብ ነበር። ትምህርት ቤቱ እሱ ከመጣ በኃላ በጣም አሻሽሎታል ተብሎ ይነገራል። እያደር ግን ብቸኝነቱ ሲበዛበት ነው መሰል ወደ እሮብ ገበያ መውጣትና ጠጅ ቤት ገብቶ ብርዝ መጠጣት እያደርም ወደ ጠጁ ተሸጋገረ። አንድ የአካባቢው ልጅ አገባና የመጀመሪያው ልጅ ተወለደ ከዛም ሁለት ሶስት ልጅ ሲደጋገም ሊቁ ውሎው ጠጅ ቤት ሆነ።

ሊቁ መጠጥ ያልጠጣ ጊዜ ብዙ ሰዎች ለምን ሃገርህ ሄደህ ዘመዶችህን ጠይቀህ አትመጣም ሲሉት መልሱ የተለመደ ነው። እነዚህን ሶስት ልጆች ይገፍ ምን ብዬ ነው ከዘመዶቼ የምቀላቀለው? ጥያቄው አልሄድ ምንም የማየውቁ የእግዜር ፍጥሮች ያሳዝኑኛል። ብቻዬን ብሄድ ደግሞ ዘመዶቼ አይለቁኝም ብሎ ሁል ግዜ እንባው ያቀራል። የሊቁ ጓደኞች ደግሞ ገረመው የሚባል የጉመሮ ሻይ ተክል መዝገብ ቤትና የትራክተር ሾፌሩ ናስር ናቸው ።

ይቀጥላል  
በልጅግ አሊ